፳፯ ው ፤ ያም፡ባልንጀራውን፡የሚ
በድል፡ገፋው፡እንዲህ፡ሲል፡አ
ንተን፡በእኛ፡ላይ፡አለቃና፡ፈራ
ጅ፡አድርጎ፡የሾመህ፡ማነው።
፳፰ ወይስ፡ትናትና፡ግብጻዊው
ን፡እንደ፡ገደልኸው፡ልትገድለ
፳፱ ኝ፡ትወዳለህን፡ ፡ሙሴ
ም፡ከዚህ፡ነገር፡የተነሣ፡ሸሽቶ
በምድያም፡አገር፡ስደተኛ፡ሁ
ኖ፡ኖረ፡በዚያም፡ሁለት፡ልጆች
፴ ወለደ፤ ዘፀ፡፪፡፲፭፤ አርባ፡ዓ
መትም፡ሲፈጸም፡የእግዚአብ
ሔር፡መልአክ፡በሲና፡ተራራ፡ም
ድረ፡በዳ፡በእሾኻም፡ቊጥቋጦ
መካከል፡በእሳት፡ነበልባል፡ተ
ገለጠለት፤ ዘፀ፡፫፡፪፡ዘዳግ፡፴፫
፴፩ ፲፯፤ ሙሴም፡ይህን፡ድንቅ፡አይ
ቶ፡ተገረመ፡ቀርቦም፡ሲመለ
ከት፡የእግዚአብሔር፡ቃል፡ወደ
፴፪ እርሱ፡መጣ፡እንዲህ፡ሲል፡፡ እኔ
የአባቶችህ፡አምላክ፡ነኝ፡የአብ
ርሃም፡አምላክ፡የይስሐቅም
አምላክ፡የያዕቆብም፡አምላክ
ሙሴም፡ተንቀጠቀጠ፡ሊመለ
ከትም፡አልደፈረም፤ ዘፀ፡፫፡፮
፴፫ እግዚአብሔርም፡አለው፡አንተ
የቆምህባት፡ስፍራ፡የተቀደ
ሰች፡ምድር፡ናትና፡የእግርህ
፴፬ ን፡ጫማ፡አውልቅ፤ በግብፅ፡
ያሉትን፡የወገኖቼን፡መከራ፡ፈ
ጽሚ፡አየሁ፡ኀዘናቸውንም፡

ሰምቼ፡ላድናቸው፡ወረድሁ፡
አሁንም፡ና፡ወደ፡ግብፅ፡እልክሃ
፴፭ ለሁ። አለቃና፡ፈራጅ፡አድርጎ
በእኛ፡ላይ፡የሾመህ፡ማነው፡ብ
ለው፡የካዱትን፡ይህነን፡ሙሴ
ን፡በቊጥቋጦ፡በታየው፡በመ
ልአኩ፡እጅ፡እግዚአብሔር፡አለ
ቃም፡መድኀኒትም፡አድርጎ፡ሰ
፴፮ ደደው፡፡ ዘፀ፡፪፡፲፬። እርሱም፡በ
ግብፅ፡ምድር፡በኤርትራ፡ባሕ
ርም፡በምድረ፡በዳም፡አርብዓ
ዓመት፡ተአምራትና፡ምልክት
እያደረገ፡አወጣቸው። ዘፀ፡፯፡፲፡
፴፯ ፲፬፡፳፩። ለ፳ልም፡ልጆች፡እግዚ
አብሔር፡አምላካችሁ፡ከወንድ
ሞቻችሁ፡እንደኔ፡ያለ፡ነቢይ፡ያ
ስነሣላችኋል፡እነርሱም፡ሰሙ
ት፡ያላቸው፡ይህ፡ሙሴ፡ነው።
፴፰ በደብረ፡ሲና፡ከተናገረው፡መ
ልአክና፡(ከአባቶ)፡ከአባቶቻቸ
ን፡ጋራ፡በምድረ፡በዳ፡በማኅበ
ሩ፡ውስጥ፡የነበረ፡ይሰጠንም
ዘንድ፡ሕያው፡የሆነውን፡ቃል፡
የተቀበለ፡ይህ፡ነው፤ ዘፀ፡፲፱፡፫
፴፱ አባቶቻችንም፡ይሰሙት፡ዘን
ድ፡አልወደዱም፡ነገር፡ግን፡እ
ንቢ፡አሉት፡በልባቸውም፡ወ
፵ ደ፡ግብፅ፡ተመለሱ፤ አሮንንም
በፊታችን፡የሚሔዱ፡አማልክ
ት፡ሥራልን፡ይህ፡ከግብፅ፡ም
ድር፡ያወጣን፡ሙሴ፡የሆነውን

